# አንድነትና ግንቦት

# 7 ፓርቲ

v²-Đ !ęÖ !T flN(!v²-Đ !ęÖ !ďÊô!

**ከፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባል**

ዛሬ በታላቋ አሜሪካ፣ በአውስትራሊያና በኔፓል፣ በቅርቡም በቬንዙዌላ ያየነው ሰላማዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች / ተቃዋሚና መንግስት/ ፉክክርና ውጤት የዘመናችን የሰላማዊ ትግል ታላቅ ድልና የድሉ ውጤት ነው:: ከዚህ ባለፈ ጥይት አልተኮሱም፣ ድንጋይ አልወረወሩም፣ የራሣቸው የሆነውን የህዝብና የመንግስት ንብረት አላወደሙም፣ ጕማ አላቃጠሉም:: ወጣቱ በስሜታዊነት እየጋለበ እንዲማገድ አላደረጉትም:: በጨዋነትና በሰላማዊነት ልዩነቶቻቸው በአገር ውስጥና በውጪ ፓርቲያቸው የሚከተለውን ፖሊሲ በሕዝብ ፊት በማንሣት የሞቀ ውይይትና ክርክር አደረጉ:: በስተመጨረሻም ሕዝብ ድምጽ ሰጠ:: የህዝብ ድምጽም የፈጣሪ ድምጽ እንዲሉ አሸነፉ ተፎካካሪዎቹም አክብረው አሸናፊነትና ተሸናፊነትን ተቀበሉ:: ዲሞክራሲ አሸነፈ፣ ሕዝብ በጉጉት የሚጠብቀውን ለውጥ ለማየት በትጋት መንቀሣቀስም ጀመረ:: ዞሮ ዞሮ ተጠቃሚው አገርና ህዝብ ነውና!

በተቃዋሚ ፓርቲ በትላንቱ ቅንጅት በዛሬውም የአንድነት ፓርቲ ውስጥ በከፍተኛ የአመራር ስፍራ ላይ እገኛለሁ:: ሰላማዊ በሆነ ትግል አማራጭ ፖሊሲዎችን በመያዝ ጠንካራ ተፎካካሪ ሁነን በመታገል ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል ብዬ አምናለሁ:: ከቅንጅት መሰነጣጠቅና መፈረካከስ በኋላ ይሄንኑ የሰላማዊ ትግል መርህ አምኜበት  በመጽናት ነው አንድነት ፓርቲን የተቀላቀልኩት:: ከተማሪነት የትግሉ ዘመን እስከተለያዩ ፓርቲዎች ትግልና ተሣትፎ በዘለቀው ቆይታዬ የኢትዮጵያ የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አነሣስና ውድቀት፣ በስሜታዊነት የሚፈጠረው የአንድ ሰሞን ሞቅታና ግርግር፣ ሕብረትና ውህደት፣ ቅንጅትና መድረክ፣ ለአገርና ለወገን ጥቅም ከመቆም ይልቅ አሣፋሪ በሆነ ሁኔታ የሚካሄደው የስልጣን ጥምና ሽኩቻ፣ እርስ በእርስ መጠላለፍና መወነጃጀል፣ አንዱ በሌላው ላይ የሚከፍተው የሃሰት ስም ማጥፋት ዘመቻና ተቀባይነት እንዳያገኝ ለማድረግ የሚካሄዱት የእርስ በእርስ ፍጭቶችና ፍልሚያዎች፣ መጠፋፋቶች፣   በየወቅቱ የሚፈጠሩት በቡድን የመከፋፈልና የአንጃ ስሜት፣ የመፈራራት ድባብ

መስፈን፣ የእኔ እበልጥ የእኔ እበልጥ ፋክክሩ እጅግ በጣም አሣፋሪና አንገት የሚያስደፋ ነው:: እንኳንስ የአገርን ኃላፊነት ተሸክሞ ለመምራት አብሮ ለመስለፍም ከባድና ትልቅ ፈተና መሆኑን በአውሮፓና አሜሪካ፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ ትግል በሰፊው አስተውያለሁ:: የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከስሜታዊነት፣ ከግንፍልና ጀብደኛ ስሜት ተላቀው «እኛ ብቻ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነን፣ ለዚህች አገር ከእኛ በላይ አሣቢና ተቆርቋሪ የለም፣ እኛ ስህተት የለብንም፣ ቃላችንም ቅዱስ ቃል ነው» ከሚለው ግዜና ትውልድ ያለፈበት ግትር አስተሣሰብ፣ የጥላቻ ፓለቲካ እራሣቸውን ለማረም፣ ለማጽዳትና ለማስተካከል ጥንካሬና ድክመታቸውን ከስሩ በመመርመርና በመፈተሽ፣ ለአዲስ አመለካከትና አስተሣሰብ፣ ለመቻቻልና ለመደማመጥ፣ ልዩነትን አክብሮ በጋራ ለመስራት እስካልቻሉ ድረስ የሚፈለገውን ለውጥ መቼም ሊያመጡ አይችሉም :: ይኼ በረዥም ዘመን ተሞክሮዬ ያረጋገጥኩት እውነት ነው ::

## ድህረ ቅንጅት-አንድነትና ወቅታዊው አደጋ

በጥቅም መፈላለግና መጋጨት፣ ማዕከላዊ አመራር ማጣት፣ መናናቅና መዘላለፍ፣ በእድሜና በትምህርት የላቀ ደረጃ ደርሰው አንቱ የተባሉትን ሁሉ አዋርዶ አጥረግርጐ አደባባይ አሰጣቸው:: ጉዳዩ በውስጥ ላለፍንበትና ለነበርንበት ሰዎች «አንቺው ታመጪው፣ አንቺው ታሮጪው» መሆኑን እናውቃለን:: የክፍፍሉንና የመበታተኑን መንስኤ በተላመደው ሁኔታ በገዥው ፓርቲ ላይ ለማላከክ ተሞከረ:: አሁንም «ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ» ነበር ነገሩ:: እነሱው ተሰባሰቡ፣ እነሱው ተበታተኑ:: ቀድሞውኑም እውነተኛና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሕዝብን የማገልገል ቅን ስሜትና ፍላጐት ቢኖርና ለስምና ለስልጣን ሽኩቻ መሽቀዳደሙ ባይኖር ኖሮ ለእዚህ ውድቀትና ውርደት ባልተበቃ ነበር:: አውሮፓና አሜሪካ የሚገኙት የዲያስፓራው ተቃዋሚዎችም ይኼንኑ የአገር ውስጥ ልዩነት መሰረት አድርገው ባህር በተሻገረው መናቆር ውስጥ ተከፋፍለው በመቆም መወነጃጀሉን ገፉበት::

ወ/ሪት ብርትኳን ሚደቅሣ በአንድ ጐራ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በሌላ ወገን ሆነው ለሽምጋይም «ለያዥ ለገናዥም» ባስቸገረ ሁኔታ እርስ በእርስ የማያባራ ፍልሚያ ያዙ:: እነ ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት የዓለም አቀፍ ቅንጅት አመራር ሆነው በኢንጂነር ኃይሉ ሻውል መሾማቸው፣ በውጪ አገር ተዋጥቶ በነሻለቃ ዮሴፍ ያዘው እጅ ነበር የተባለው 3.5 ሚሊዮን ዶላር መጥፋት፣ ኢንጂነሩ ከሻለቃ ዮሴፍ ያዘው የሰጡት ድጋፍ የአጣሪ ኮሚቴ «ይሰየም አይሰየም?» ጥያቄና ከውጪ ለታሰሩት ቅንጅቶች የሚላከው የእርዳታ ገንዘብ በሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ አማካይነት በአግባቡ እንደማይከፋፈልና መጠቃቀምና ልዩነት እንደነበር መገለፁ ሽኩቻውን አሰፋት:: እነ ወ/ሪት ብርትኳን የአውሮፓን ጉብኝት ጨርሰው ወደ አገር ቤት ከተመለሱና ትንሽ ከቆዩ በኋላ የቀድሞውን መዐህድ በኋላ መኢአድ ቢሮ በቅንጅት ለጋራ ቢሮነት ይጠቀሙበት ስለነበር ቅራኔውም እየተካረረ ሄደ:: አቶ አባይነህ ብርሃኑ «የኢንጂነሩ ተወካይ እኔ ነኝ» በማለት እነ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ዶ/ር ኃይሉ አርአያ፣ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ፣ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም ፣ዶ/ር ያዕቆብ ወ/ማርያም ሌሎችንም ቢሮ እንዳይገቡ ከለከሏቸው:: ታገዱ:: እነሱም ቢሮ

ፈልገው ደጋፊዎቻቸውን አሰባስበው የአንድነት ፓርቲን ፍቃድ አውጥተው ስራ ጀመሩ:: ይህ ሁሉ ውጣ ውረድና ምስቅልቅል የሚያሳየን በተለያየ ጊዜ የሚነሱት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ካለፈው ውድቀትና ስህተት ለመማር ያልቻሉ ገና ብዙ ብስለት የሚቀራቸው እራሳቸውን መገምገምና ማረም የተሳናቸው መሆኑን ነው::

በአንድ እጅ መስቀል፣በአንድ እጅ ሰይፍ!

በአሁኑ ሰዓት በአንድነት ፓርቲ ውስጥ በገሀድ የሚታይና የገዘፈ ትልቅ ችግር ተከስቷል:: ይህም ከላይ በተለያየ መልኩ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የአንድነት ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣ የማዕከላዊው ኮሚቴ ወይንም የማዕከላዊ ምክር ቤት አባላትና ወረዳም በክፍለ ሀገራት፣በአዲስ አበባ፣ዞን ወረዳና ቀበሌ በተዋቀሩት የአመራርና የመሰረታዊ ድርጅት አባላት ውስጥ ከአናት ያለውን የፖለቲካ አመለካከት ተከትሎ ሰፊ ልዩነቶች እየታዩ ነው:: ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ ሌሎችም ህገ መንግስቱንና ህጉን አክብረውና አስከብረው እንደሚንቀሳቀሱና እንደሚሰሩ በተለያዩ መድረኮች ገልፀዋል:: ብቸኛና አማራጭ የሌለው የትግል ስልታቸው ሰላማዊ ትግል መሆኑን በቃል ይግለፁ እንጂ በተግባርና በሰላም ሽፋን ከጀርባ የሚካሂዷቸው እንቅስቃሴዎች በአንድነት ፓርቲ ላይ የቀይ መብራት የአደጋ ምልክት እየበሩበት መሆኑን፤ ለሁሉም ሀገርና ሰላም ወዳድ ወገኔ፣ለሁሉም ኢትዮጵያዊ መግለፅ እወዳለሁ:: የጥሩው ተጠቃሚ፣ የመጥፎው ውጤት ተጎጂም እኛው ነንና::

በአንድነት ፓርቲ ህጋዊና ሰላማዊ ፍቃድ ስር ታቅፈው ከሚንቀሳቀሱት አመራሮችና አባላት ውስጥ «ግንቦት 7» እያለ እራሱን በሚጠራውና በዶ/ር ብርሀኑ ነጋ፣ሙሉነህ እዮኤል፣መስፍን አማን እና ሌሎችም በሚመራውና ተቀማጭነቱን በአሜሪካን ሀገር በማድረግ የትጥቅ ትግልን ብቸኛ አማራጭ አድርጎ በመንግስት ላይ ጦርነት ካወጀው ኃይል ጋር በስውር ተቀናጅተው፣ ከነሙሉነህ ኢዮኤል አመራር በመቀበል የገንዘብና የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ እያገኙ ሽፍን ዓላማ ይዘው በአንድነት ፓርቲ ውስጥ መሽገው የሚንቀሳቀሱ ወገኖች አሉ፡ «በአንድ እጅ መስቀል፣ በአንድ እጅ ሰይፍ» ያልኩበትም መሰረታዊ ምክንያት ይኸው ነው:: በዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የሚመራውን ግንቦት 7 የተባለ ጦርነት ያወጀ ድርጅት ከአዲስ አበባ በመሄድ የተቀላቀሉት የቀድሞው የቅንጅት ዋና ፀሀፊ ሙሉነህ ኢዮኤል በአሁኑ ሰዓት በውጭ ሀገር ሆነው የአንድነት ፓርቲ ተወካይና ተጠሪ ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ:: በግንቦት 7 ፓርቲ ውስጥ አንድነት ፓርቲ ታቅፏል? በግንቦት 7 ፓርቲ ውስጥ አንድነት ፓርቲን መወከልና ተጠሪ መሆን ለምን አስፈለገ? ይህን ጉዳይ የሚያውቁት የተወሰኑ የአንድነት ፓርቲ ስራ አስፈፃሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት. እንዲሁም በደረጃ ከዚህ ውስጥ ያልተካተቱ ግን ደግሞ ለምስጢሩ ቅርብ የሆኑ የታች አካላት ድርጅታዊ ስራቸውን ከዚህ አኳያ ለማከናወን ሌሊት ከቀን እየተራወጡ ይገኛሉ:: የቀንና የሌሊት ስብሰባዎችን በግለሰብ ቤቶችና በሆቴል እያደሩ ጭምር ያደርጋሉ:: ስልክ እየደወሉ ክፍለ ሀገርም እየተንቀሳቀሱ ተመሳሳይ ስራ ይሰራሉ፡ በእርግጠኝነት ሰላማዊ ትግልን ከልቡ የሚደግፈው አብዛኛው የአንድነት ፓርቲ አባልና ደጋፊ ይህን ሲሰማ ያዝናል:: በስሙ እየተነገደበት እንደሆነም ይረዳል::

አላስፈላጊ ለሆነ መስዋዕትነት ቅን ዜጎችን እያዘጋጁዋቸው መሆኑንም ይገነዘባል:: በየሰንበቴ ቤቱ ሳይቀር ምን እንደሚሰራም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች ምን በመስራት ላይ እንዳለ ሰላማዊ ትግልን ከልብ

አምኖበት የተሰለፈው የአንድነት ፓርቲ አባል አያውቅም። የጉዳቱ ተጠቂና የችግሩ ሰለባ የሚሆነው በኃላ በሚመጣው የጦስ ችግር ውስጥ የመግባት ጣጣ ነው። ንፁሀንን እየማገዱ ዳር ሆነው በመሳለቅ የእርዳታና የገንዘብ ማሰባሰቢያ እርጥባን መለመኚያ አድርገውታል። በድህው ስምና ጉዳት እየነገዱና እየቸረቸሩ እያተረፉም በአውሮፓና አሜሪካ የተንደላቀቀ ህይወትን መኖር የለመዱት የፖለቲካ ወስላቶች ሽፍንፍናቸው ሲገለጥ በቃችሁም ሊባሉ ይገባል። አዲስ አበባ ከሚገኙት አንዳንድ የአንድነት ፓርቲ ስራ አስፈፃሚዎችና የምክር ቤት አባላት የተለያዩ ስብሰባዎች ለመታዘብ የቻልኩት ሰላማዊ ትግል ሳይሆን ጦርነት ያወጀውን የግንቦት 7 ፓርቲን ዓላማዎች ማንፀባረቅ ነው። ከዚያ በስተቀር ህጉን አክብረው በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ ያላቸው ዝግጁነት በተመናመነ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ለመገንዘብ አስችሎኛል።

ዋቢ ለመጥቀስ ያህል እነ አቶ አምሀ በተደጋጋሚ «የሰላማዊ መንገዱ በር ተዘግቷል፤ ድርጅቱ መበተን አለበት» ማለታቸው፣ በቅርቡም ዶ/ር ኃይሉ አርአያና አቶ ታምራት ታረቀኝ የወ/ት ብርቱካን ሚዲቅሳን መታሰር አስመልክተው ያወጡት መግለጫ የአቶ አምሀን ኃሳብ ሳይቀየር እንደደገፉት ያሳያል፣ ማረጋገጫም ነው።

የነኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው እና የእነ ዶ/ር ያዕቆብ ወ/ማርያም ወጣ ገባ ማለት፣ የተከበሩ አቶ ተመስገን ዘውዴ፣አቶ አለባቸው አያሌው፣ አቶ ንጉሴ ነውጤ፣አቶ መላኩ ተፈራ፣አቶ እንዳሻው እምሻው፣ ወ/ሮ ሽዋዬ ኪሮስ፣ ወ/ሮ ለቃች ደገፋ፣ አቶ ይልቃል ጌትነት፣ አቶ ቃለአብ ወረዳና ሌሎቹም ቡድኖችና ግሩፕ በመያዝ የአንድነት ፓርቲን ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንደ ሽፋን በመጠቀም የተለየ ተልዕኮ ለመፈፀም በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኙ በሚደረጉት ስብሰባዎች በሚቀርቡት ሀሳቦች እንዲሁም እርስ በእርስ በሚደረጉ ጫዋታዎችና ቅርርቦች ተመልክቻለሁ። የአንድነት ፓርቲ አመራር በሁለት ቡድን ተከፍሎና ተሰንጥቆ ሰላምን በሚደግፍና ጦርነትን በሚያቀነቅኑ ኃይሎች መካከል በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ችያለሁ። በእነዚህ መሰረታዊ ምክንያቶች ፓርቲው በአደጋ ላይ እንደሚገኝ ማንኛውም ሰላም ፈላጊና ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊ እውነቱን እንዲረዳውና እንዲገነዘበው ማድረግ ግዴታዬ መሆኑን አምናለሁ።

ከቅርብ ግዜ ወዲህም ከወ/ት ብርቱካን ሚዲቅሳ መታሰር ጋር በተያያዘ እየታየ ያለው አዝማሚያም ውስጥ ለውስጥ ተዳፍኖ የነበረውን ጉዳይ አፈንድቶ ሌላው በግልፅ እንዲያየው ከማድረግ ውጭ እዛው ለነበርን ሰዎች ብዙም አዲስ ነገር አልነበረም። ወ/ት ብርቱካን ሚዲቅሳ ድርጅቱን ሲመሩም «ሰላማዊ መንገድን በብቸኛ አማራጭነት በመያዝ ይንቀሳቀሱ ነበር» ቢባልም በእኔ በኩል ምንም ተቀባይነት የለውም። አምነውና ፈርመው በአደባባይ ህዝብ አውቆት ፀሀይ ሞቆት ይቅርታ ጠይቀው የወጡበትን ጉዳይ እንደገና ወደ መካድ መረማመድ ዳግም ሁከትና ብጥብጥ ግርግር የመፍጠር ጥረት በመሆኑ መከራከር አይቻልም። ይህ ጉዳይ በስራ አስፈፃሚ ስብሰባ ወ/ሮ ብርቱካን ባሉበት ተነስቶ እነ አስቻለው ከተማ፣ዶ/ር ሀይሉ፣ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው፣ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም እና አቶ የኔነህ ሙላት በስብሰባ «አብረን በግልፅ ይቅርታ ጠይቀን ነበር የወጣነው። ይህ ጉዳይ የራስሽ ብቻ ነው» በማለት እኛ በድጋሚ መታሰር አንፈልግም» እስከ ማለት ደርሰው ነበር። ስብሰባውን ረግጦ ከመውጣት እስከ መልቀቂያ መፃፍ

እነ ዶ/ር ያዕቆብ እነ የኔነህ ሙላት አልደረሱም? ለምንድነው ህዝቡን የምናሳስተው? ወዳልሆነ ነገር የምናስገባቸው?

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሀቅ ቢኖርም፣ ሰላም ፈላጊዎች የሆኑ ድርጅቱ አመራሮች ጉዳዩን ቢያውቁትም፣ ከላይ ለመግለፅና ማንነቱን ለማሳየት በሞከርኩት ቡድን እንጎዳለን የሚል ስጋት ስላላቸው ሀሳባቸውን በነፃነት ከመግለፅ ይልቅ ዝምታን መርጠዋል፡፡

የአንድነት ፓርቲ አመራር ከቅርብ ግዜ ወዲህ ዳግም የድርጅቱን መሰረታዊ ህልውና የሚፈታተን ፈተና ገጥሞታል፡፡ ከትላንቱ የቅንጅት አነሳስና ውድቀት ታሪክ ባለመማር አንዳንድ የአንድነት ፓርቲ አመራር አካላት ፓርቲው «መድረክ» የተባለው የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሰብስብ አባል እንዲሆን ግፊት እያደረጉና እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ የአንድነት ፓርቲ አንድነትን በፅናት የሚደግፍና የሚያራምድ ሆኖ ሳለ በውስጣቸው የመገንጠል ዓላማን ይዘው በስውርና በሽፋን ከኦነግ ጋር ከሚንቀሳቀሱ ኦፌዲንን ከመሳሰሉ ድርጅቶች ጋር ነው አንድነት /ውህደት/ መስርተን እንንቀሳቀስ የሚሉት፡፡ ይህም የአንድንት ፓርቲ መሰረታዊ ዓላማ የሚፃረር ነው፡፡ በእዚሁ «መድረክ» በተባለው ስብስብ ውስጥ ተጠልለው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት እነ ስየ አብርሃና እነ ገብሩ አስራትን ብንወሰድ እነዚህ ሰዎች እውነት የህዝቡ ችግር ገብቷቸው ነው የፖለቲካ ድርጅት መስርተው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉት? ወይንስ በተለያየ መንገድ ያጡትን የፖለቲካ ስልጣን መልሠው ለማግኘት ነው በሽፋን እየሰሩ ያሉት? ከእናት ድርጅታቸው ኢህአዴግ የሚለያቸው ዋነኛ ነጥብ ምንድነው? በፍፁም ግልፅ አይደለም፡፡

የአንድነት ፓርቲ ከእነዚህ ወገኖች ጋር በመድረክ አሰባሳቢነት ተጠልሎ ለመስራት መፈለጉ ዋነኛ ስትራቴጂካዊ ዓላማው ለስልጣን እንጂ ለህዝብ የሚደረግ ትግል አለመሆኑን የሚያረጋግጥልን ነው፡፡ ይህም የጉዳዩ አሳሳቢነትና በአንድነት ፓርቲ አባላት አማካይነት በተደጋጋሚ እየተነሳ ሲሆን በተወሰኑ አመራሮች አማካይነት ሀሳቡ ተቀባይነት እያጣ ነው፡፡ መሰረትም የለውም፡፡ የአንድነት ፓርቲ የራሱ ዓላማና ግብ ያለው ድርጅት እንጂ የማንም ስልጣን ፈላጊ መወጣጫ አይሆንም ነው ማለት የምፈልገው፡፡ አንድነት ፓርቲ ሰላም የሚፈልግ ድርጅት ነው፡፡ መንግስትም ሊገነዘብልን የሚገባው ነገር ቢኖር ይህ ነው፡፡ አመራሩንም በጅምላ መፈረጅ የለበትም ብዙ አመራሮች ሰላማዊ መንገድን የሚፈልጉ እንዳሉ ከአባላትም ዘንድ ተመሳሳይ ፍላጎት እንዳለ መንግስት ሊያውቀው ይገባል፡፡ ሁሉንም በጅምላ መምታት አያስፈልግም፡፡ እኔ ይኸንን ፅሁፍ ለመፃፍ የተገደድኩበት ምክንያት ድርጅቱ አደጋ ላይ እንዳለ ከመጀመሪያው አዝማሚያውና አካሄዱ በጣም ያስፈራኝ ነበር፡፡ ሊመጣና ሊከተል የሚችለውንም ነገር እገምት ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በውስጥ የማያቸውን ሁኔታዎች አደገኛነት ለኢትዮ ቻናል ጋዜጣ እፅፍ ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን አልረፈደም፡፡ የአንድነት አመራሮችና የአንዳንድ አባላት ሰላምና ጦርነትን አቀናጅተው መጓዝ እንደማይችሉ፣ እንደማይገባም አምናለሁ፡፡ የግዴታ ሰልፋቸውን ማስተካከልንና ብቸኛ ውን የሰላም ጎዳናም መምረጥ አለባቸው፡፡